# <u>የመዋለ ሕጻናት ትምህርት ቦርድ</u>

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ቀን/Day 1 | ቀለም-ያላቸው የተለያዩ በእጃችሁ-ሙሉ አፍሳችሁ-ያዙ (ሴሪያል/cereal፣ ቁልፎች/buttons፣ ብሎክስ/blocks) ሁሉንም ቁጠሩ - በየቀለማቸው ለዩ የእያንዳንዱ-ቀለም ስብስብን፣ ቁጠሩ *የእናንተን 'tens frames' መጠቀም ትችላላችሁ።* | ለጓደኛ ወይም ለቤተሰብ አባል፣ አንድ-መልካም ነገር አድርጉ። ምን-ዓይነት ስሜት እንደሚሰማቸው፣ አስቡ። | ወደ-ውጪ ተመልከቱ። የአየር-ጠባይ ምልከታችሁን መዝግቡ። ስለአያችሁት-ነገር ስዕል ስሉ። | ከትልልቅ-ሰዎች ጋር ሆናችሁ፣ መክሰስ (snack) ስሩ። እነዚህን ቃላቶች በመጠቀም - "በመጀመሪያ፣ በመቀጠል፣ ከዚያ-በኋላ፣ እና በመጨረሻ (first, next, then, and last)" የሚሉትን የእርምጃ-አካሄዶችን - ሣሉ ወይም ወደ ታች-ፃፉ። | ለትልልቅ-ሰዎች፣ በትምህርት ቤት ውስጥ የተማራችሁን መዝሙር ዘምሩላቸው። ምሳሌ: የዓመቱን ወራቶች፣ ወይም በሣምንት ውስጥ ያሉትን ቀናቶች። |
| ቀን/Day 2 | ስንት ቁጥሮች መጻፍ ይችላሉ? ቁጥሮችን በወረቀት ላይ ይፃፉ ወይም በአሸዋ ወይም በሩዝ ይሳሉ. የእርስዎን '120 Chart' መጠቀም ይችላሉ። | እራሳችሁን ለመግለጽ፣ 3 ቃላት (words) አስቡ። ምንድነው፣ ልዩ (special) የሚያደርጋችሁ-ነገር? | ውጪ-ውጡ እና በመረማመጃ-መንገዱ ላይ አንድ-መቅጂያ (jug) ውሃ አፍስሱ። በየትኛው-አቅጣጫ ውሃው ይፈሳል? እንጨት-ተጠቅማችሁ ወይም ሌላ ዕቃዎችን ተጠቅማችሁ፣ አቅጣጫውን እንዲቀይር ማድረግ-ትችላላችሁ? | ከትልልቅ-ሰዎች ጋር ሆናችሁ፣ ልብ-ወለድ ታሪኮች (fiction story) ማንበብ። ስለገጸ-ባህሪያቶቹ፣ አቀማመጡ፣ እና ስለችግሩ እና ስለመፍትሄው ንገሯቸው። | የፑሽአፕ/ፕላንክ (pushup/plank) እየሰራችሁ ባላችሁበት ጊዜ፣ ለ1 ደቂቃ በምትቆዩበት ጊዜ፣ መዝሙር ዘምሩ። |
| ቀን/Day 3 | አብረን-እንንቀሳቀስ። 'ጃምፒንግ ጃክስ/jumping jacks' ለማድረግ ሞክሩ፤ ይህም ወደላይ በመዘርጋት እና ወደታች የእግር-ጣቶችን በመንካት፣ ኳስ በማንጠር (bouncing a ball)፣ ወይም በአንድ-እግር በመዝለል ነው። እያደረጋችሁ-ባላችሁበት ጊዜ፣ ቁጠሩ። እስከ-ስንት ድረስ ቆጠራችሁ? | በቤት-ውስጥ የተሰራ ስጦታ ለአንድ-ሰው አዘጋጁ። አብሮት-የሚሄድ ማስታወሻ-ፃፉ። | ስለ መግፋት እና በመሳብ (pushes and pulls) የተማራችሁን በመጠቀም፣ የቤት-ውስጥ ቦሊንግ (indoor bowling) ጨዋታን-ተጫወቱ። የፕላስቲክ የቦሊንግ ቋሚዎችን ወይም በቤት-ውስጥ ለመጠቀም ደህና-የሆኑ ኳሶችን ተጠቀሙ። | በቤታችሁ-ውስጥ ቢያንስ 10 የተለያዩ-ነገሮችን ፈልጉ። የእያንዳንዳቸውን ስም-ተናገሩ። የእያንዳንዱን ዕቃ - እንደየ ቃሉ ድምጽ መሠረት አድርጎ፣ የመጀመሪያ እና የመጨረሻ ፊደላቸውን መፃፍ-ትችላላችሁ? ለምሳሌ: "DOG" – የመጀመሪያው ድምፁ "d" ነው፣ እና የመጨረሻ-ድምፅ "g" ነው። | በቤታችሁ-ዙሪያ፣ 3 ጊዜ - የ'Crabwalk' አድርጉ። |

*Alexandria City Public Schools Amharic Kindergarten*

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ቀን/Day 4 | ሦስት-ማዕዘኖች (triangles)፣ ክቦች (circles)፣ አራት-ማዕዘኖች (rectangles)ን እና ካሬዎች (squares)ን በመጠቀም፣ ስዕልን ሳሉ። በስዕላችሁ-ላይ፣ ከእያንዳንዱ ምን ያህሎችን - ተጠቅማችኋል? | በቤት-ውስጥ፣ አንድን-ሰው በቤት-ውስጥ ስራ (chore) አግዙ። | ፈቃድ-ጠይቃችሁ፤ ውጪ-ሂዱ እና የራሳቹ-ጥላ (shadow) ላይ ተመልከቱ። ከዚያ-በመቀጠል፤ ቆይታችሁ በዚያኑ ቀኑ-ላይ ውጪ-ሂዱ እና ለውጦች-እንዳሉ ተመልከቱ። ለአዋቂ-ሰው፤ ጥላዎች (shadows) እንዴት እንደሚፈጠሩ፣ ንገሩዋቸው። | በመኖሪያ-ቤታችሁ ውስጥ ‘treasure hunt’ ለማድረግ ሂዱ፣ እና በእያንዳንዱ የፊደል-ተርታ (alphabet) የሚጀምሩ ዕቃዎችን - ፈልጉ። | ከእናንተ-ጋር በቤታችሁ ውስጥ ለሚኖር-ሰው፣ ስዕል መሣል። በፊት-ላይ (face) ያሉትን ሁሉንም ክፍሎች ማካተታችሁን-እርግጠኛ ሁኑ። |
| ቀን/Day 5 | በብሎኮች/blocks፣ በሌጎስ/Legos ወይም በሌካ የመገንቢያ መጫወቻዎች - ግንብ/tower-ገንቡ። በግንቡ/tower ውስጥ፣ ምን-ያህል ዕቃዎች እንዳሉ - ቁጠሩ። ሌላ ግንብ/tower ገንቡ። ሌላ-ምን ልትቆጥሩ፣ ትችላላችሁ? *የእናንተን፣ ‘tens frames’ መጠቀም ትችላላችሁ።* | ምንም-ባልተፃፈበት ወረቀት ላይ - “How to Be a Good Friend” መጽሐፍን - ፍጠሩ። ጥሩ-ጓደኛ ለመሆን እንዴት እንደምትችሉ፤ ቃላቶችን እና ምስሎችን በመጠቀም አሳዩ። | በመኖሪያ-ቤታችሁ ውስጥ፣ የምትወዱን ነገር ፈልጉ። ከዚያም፤ ከምትወዱት-ዕቃ የበለጠ ከባድ-የሆኑ አምስት-ነገሮችን እና ቀላል-የሆኑ አምስት-ነገሮችን - በቤታችሁ ውስጥ ለመፈለጉ-ሂዱ። | በመኖሪያ-ቤታችሁ ውስጥ፣ የምትወዱትን መጽሐፍት አንስታችሁ፣ ወደ በልዩ-ሁኔታ “የንባብ-ቦታ/reading spot” ወደሆነው ቦታ ሄዳችሁ - አንብቡ። ከአንድ-ሰው ጋር፣ በታሪኩ ውስጥ የምትወዱትን ክፍል አጋሩ። | መጽሐፉን በጭንቅላታችሁ ላይ ሚዛኑን-እንዲጠብቅ አድርጋችሁ፣ አምስት-ጊዜ - በክፍሉ ዙሪያ በቀስታ ተራመዱ። |
| ቀን/Day 6 | ከዜሮ (0) እስከ ሃያ (20)፣ አንድ ቁጥርን ምረጡ። ያንን-ቁጥር የሚወክለውን ምስል/picture፣ ሣሉ። ከምስላችሁ/picture አጠገብ ቁጥሩን ለመፃፍ ሞክሩ። | የምትወዱት በዓል (holiday) ምንድነው? ለምን-አስፈላጊ እንደሆነላችሁ፣ ስዕል-ሳሉ፣ ፃፉ፣ ወይም ተናገሩ። | ፈቃድ-ጠይቃችሁ፤ ውጪ-ሂዱ እና አምስቱን የስሜት-ህዋሳችን በመጠቀም ምን-እንዳያችሁ፣ እንደተሰማችሁ፣ እንደቀመሳችሁ፣ እንደነካችሁ እና እንደሰማችሁ ግለጹ! | ዛሬ ምን እንዳደረጋችሁ፣ ስዕል ለመሣል እና ዓረፍተ-ነገር ለመፃፍ፣ ጆርናል ፍጠሩ። | በቤታችሁ ውስጥ ያገኛችሁት ነገር ረጅም/አጭር ድምጽ የመኖር ፓተርኖች (patterns) ላይ ተጫወቱ (ለምሳሌ፤ ከኩባያው ጎን-ላይ እርሳስ ለጥፉ)። |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ቀን/Day 7 | በቤት-ዙሪያ የሚገኙ የተለያዩ-ነገሮችን በመጠቀም፣ ቅርፆችን መገንባት። (playdoh, sticks, forks, string or yarn, rolled towels) | ስለ ትምህርት ቤታችሁ፣ ማህበረሰባችሁ ወይም ሃገራችሁ - ለመለወጥ ስለምትፈልጉት፣ እና ለምን-እንደሆነ፤ ስለ አንድ-ነገር አስቡ። ስለ ሃሳባችሁ፣ ለአንድ-ሰው ንገሩ። | በመኖሪያ-ቤታችሁ ውስጥ ያሉ ዕቃዎችን፣ ወይም የራሳችሁንም ጣቶች ቢሆን ተጠቅማችሁ፣ የአሻንጉሊት ጥላዎች (shadow puppets)ን ስሩ። በ'አሻንጉሊት ጥላዎች (shadow puppets)' ታሪክ-መተረክ ትችላላችሁ? | Read with a buddy! ታሪኩን፣ ከወላጅ፣ እህትና-ወንድ፣ ጓደኛ፣ ወይም በውስጡ-የተሞላ እንስሳ/stuffed animal ጋር አጋሩ። የምትወዱትን ገጽ፣ በትወና-አሳዩ። | ሠውነታችሁን-ተጠቅማችሁ፣ የመጀመሪያ-ስማችሁን ስፔል-ለማድረግ (to spell your first name) የፊደል ቅርፆችን ስሩ። |
| ቀን/Day 8 | በ1'ዎሽ፣ እስከምትችሉት ድረስ ቁጠሩ። እስከ-ስንት ድረስ መቁጠር ቻላችሁ? የ'120 Chart'ን በመጠቀም የመቁጠር ልምምድ አድርጉ። | በማህበረሰቡ-ውስጥ እርዳታ ስለሚያደርጉ አስቡ እና የሚያደርጉትን አስተዋጽዖ አስቡ። የምስጋና ማስታወሻ የሚሆን ስዕል-ሣሉ ወይም ፃፉ። | ወደ-ውጪ ተመልከቱ እና የአየር-ሁኔታው ላይ ምልከታ-አድርጉ። የተመለከታችሁን-ነገር፣ በስዕል ሣሉ። ከትናንትናው የአየር-ጠባይ የተለየበትን መንገድ እና አንድ-ዓይነት የሆነበትን መንገድ፤ ፈልጉ። | ስለ መኸር 5 ጥሩ ነገሮችን ይዘርዝሩ። | ለመዝሙሩ ዳንስ-ፍጠሩለት እና በቤታችሁ ውስጥ ለሚገኝ ሰው አቅርቡና-አሳዩ። |
| ቀን/Day 9 | በመኖሪያ-ቤታችሁ ውስጥ፣ 'ካሬዎች/squares'፣ 'አራት-ማዕዘኖች/rectangles'፣ 'ክቦች/circles'፣ እና 'ሦስት-ማዕዘኖች/triangles'ን - ፈልጉ። እያንዳንዱ ቅርጽ ምን-ያህል ጎኖች/sides እና ጫፎች/vertices አላቸው? | በመኖሪያ-ቤታችሁ ውስጥ፣ ስለሚኖር ዕቃ/object አስቡ። የሚገኝበትን-ቦታ በመግለጽ፣ የቤተሰብ አባሉ - ስለምን-ዕቃ እንደምትገልጹ እንዲገምቱ ለማድረግ ሞክሩ። እንደ *next to, near, in front of, above, below* ያሉትን ቃላቶች ተጠቀሙ። | የቤት ውስጥ ዕቃዎችን ለማጠብ፣ በቤታችሁ-ውስጥ አዋቂ-ሰውን እርዱ። የተለያዩ ነገሮች እያጠባችሁ ባላችሁበት ጊዜ፣ ውሃው የሚወርድበትን አቅጣጫ አመልክቱ-እና ግለጹ። | ንጽህ-በሆነው የእጅ-ጽሁፋችሁን ተጠቅማችሁ፣ ስማችሁን አራት-ጊዜ ፃፉ። በቤታችሁ-ውስጥ፣ የእናንተ-በሆኑ ዕቃዎች ላይ ስማችሁም ለጥፉበት! | ሚዛን-ለመጠበቅ የሚያስችላችሁን - የተለያየ መንገዶች ቁጠሩ። አንዳንድ-ሃሳብ እንዲሰጥ፤ የአንድ-እግር/አንድ እጅ፣ ሁለት እጆች፣ ወይም አንድ እግር - ያሉትን ሞክሩ። |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ቀን/Day 10 | ወደ 'shape Hunt' ሂዱ! ምን ያህል ቅርፆችን ማግኘት ቻላችሁ? ስለአገኛችሁት ነገር ፎተግራፎች-ውሰዱ ወይም ስዕሎችን ሣል። | በበጋ (summer) ወቅት ያላችሁበት-ሁኔታ የሚያሳይ እና በክረምት (winter) ያላችሁበትን-ሁኔታ የሚያሳይ - የራሳችሁን ምስል - ሳሉ። ምስሎቹ (pictures) እንዴት እና ለምን የተለያዩ እንደሆኑ አስቡ። | ወደ ውጪ ሂዱ እና፣ እንደ እንጨቶች/sticks፣ ቅጠሎች/leaves፣ ድንጋዮች/rocks ወዘተ..ያሉትን አስር-ነገሮች ሰብስቡ። በመጀመሪያ በየእቃው-ዓይነት፣ ከዚያ ስትነኩት-በሚሰጠው ስሜት - ሻካራ ወይም ለስላሳ በመሆኑ - ለዩዋቸው። ከዚያ-ደግሞ፣ ዕቃዎችን በመጠን ለዩ - ትልቅ ወይም ትንሽ - ናቸውን? | ተመራጭ-በሆነው ታሪክ-የመተረክ ድምፃችሁን ተጠቅማችሁ መጽሐፍን ለማንበብ፣ በድጋሚ-ለማንበብ ልምምድ-አድርጉ። ወላጆችሁ በስልካቸው ሊቀዷችሁ-የሚችሉ ከሆነ፣ ስታነብቡ ያለውን ቪዲዮ ለዘመድ ወይም ለጓደኛ ላኩ! | ስዕል-በመሣል ወይም በቤታችሁ አካባቢ የሚገኙ-ነገሮችን ተጠቅማችሁ፤ ለመጎብኘት-የምትፈልጉትን ቦታ-እይታ ፈጥራችሁ-አሳዩ (ለምሳሌ፤ የውሃ-ዳር/beach፣ ተራራዎች/mountains፣ የመዋኛ-ቦታ/pool፣ ፓርክ) |
| ተጨማሪ ምርጫዎች | በቤተሰብ-አባል ወይም ከዩቲዩብ (YouTube) ላይ፣ ድምጽ-ከፍ ተደርጎ መጽሐፍ ሲነበብ አዳምጡ። ስለ መጽሐፉ-ያላችሁን ጥያቄ ፃፉ። (ለምን-ይህ እንደሆነ እስባለሁ/*I wonder why...*) | በመኖሪያ-ቤታችሁ ውስጥ፤ ዕቃዎችን ወይም ቦታዎችን ለመሰየም ምልክቶችን አድርጉ! | ስለ መኸር 5 መጥፎዎቹን ይዘርዝሩ። | በ'finger-stretch' እነዚህን ቃላቶች እንዴት መስራት እንደሚቻል በቤተሰባችሁ ውስጥ ለሚገኝ-ሰው አስተምሩ: *mom, dad, cat, fish* | ከአንድ-ሰው ጋር ስለ መጽሐፍ የንግግር-ውይይትን በማድረግ አስጀምሩ። የቤተሰብ አባላችሁን፣ ወይም ጎረቤታችሁን - ስለሚወዱት መጽሐፍ ጠይቋቸው! |

# 120 Chart

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
| 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 |
| 21 | 22 | 23 | 24 | 25 | 26 | 27 | 28 | 29 | 30 |
| 31 | 32 | 33 | 34 | 35 | 36 | 37 | 38 | 39 | 40 |
| 41 | 42 | 43 | 44 | 45 | 46 | 47 | 48 | 49 | 50 |
| 51 | 52 | 53 | 54 | 55 | 56 | 57 | 58 | 59 | 60 |
| 61 | 62 | 63 | 64 | 65 | 66 | 67 | 68 | 69 | 70 |
| 71 | 72 | 73 | 74 | 75 | 76 | 77 | 78 | 79 | 80 |
| 81 | 82 | 83 | 84 | 85 | 86 | 87 | 88 | 89 | 90 |
| 91 | 92 | 93 | 94 | 95 | 96 | 97 | 98 | 99 | 100 |
| 101 | 102 | 103 | 104 | 105 | 106 | 107 | 108 | 109 | 110 |
| 111 | 112 | 113 | 114 | 115 | 116 | 117 | 118 | 119 | 120 |

# Tens Frames

